## የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት

- የሀገሪቱን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስትራቴጂ መሰረት በያደርጋል ከመስሪያ ቤቱ ተልዕኮ ጋር የሚጣጣም የመ/ቤቱን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስትራቴጂና መሪ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ይከታተላል፤ በየጊዜውም እንዳስፈላጊነቱ ማሻሻያ ያደርጋል ፤
- በመስሪያ ቤቱ የበላይ አመራር በሚሰጠው የሥልጣን ውክልና መሠረት በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል ወይም የሚሰጡ ውሳኔዎችን ተግባራዊነት ይከታተላል፣
- በመስሪያ ቤቱ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ ማሻሻያና ማስፋፊያ የሚፈልጉ አዳዲስ ፍላጎቶች ሲኖሩ ተገቢውን ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ተግባራዊ ያደርጋል ፣ ይከታተላል፤
- የአዳዲስና ነባር የኔትወርክ ሲስተሞች የጥራት ደረጃ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ የሚያስችሉ መንገዶችን መቀየስ፤
- የመስሪያ ቤቱን ድረ-ገፅ ከህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ጋር ተቀናጅቶ ማደራጀትና አዳዲስ አሠራሮችን በየጊዜው በማካተት ትክክለኛና ወቅታዊ የመረጃ ፍሰት ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ያደርጋል ፣
- የመስሪያ ቤቱን የመረጃ ፍሰት ዓይነትና መጠን የመለየት ጥናት ስራ ሲካሄድ ከህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፣ ይከታተላል፤
- በመረጃ ቋቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን በመለየት ወቅታዊ የሆኑ የመከላከያ ሶፍትዌሮችና የሴኩሪቲ ሲስተሞችን ማደራጀት፤ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፡
- የመሥሪያ ቤቱን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችን፣ መረጃዎችን፤ የሃርድዌርና የሶፍትዌር፤ የዳታ ሴንተር እና አጠቃላይ የአይሲቲ ሃብቶች ደህንነት የሚጠበቁበትን መንገድ ያመቻቻል፤ ማዘጋጀት፤ ማደራጀትና ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
- የሶፍትዌር ላይሰንስና የመረጃዎች ቅጅ በአግባቡ መያዙን ክትትል ያደርጋል ፤
- የአይሲቲ ኘሮጀክቶችን ማቀድ፣ መፍትሄ አቅራቢ ድርጅቶችን በመጋበዝና በመምረጥ ሂደት መሳተፍ እና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኘሮጀክቶችን ማስተዳድር፤
- ለመስሪያ ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት የሚውሉ የሶፍትዌር፣ ሃርድዌር እና ሌሎች ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች ስፔስፊኬሽን

ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣ በትክክል መስራታቸዉንና አገልግሎት ላይ መዋላቸውን በበላይነት መቆጣጠር፣

- ❖ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች ኢሜል፣ ኢንተርኔት ወዘተ…ተጠቃሚ እንዲሆኑ የአጠቃቀምና የስልጠና ማንዋል በማዘጋጀት ለሠራተኞች መሰረታዊ የኮምፒውተር አጠቃቀም ሥልጠና ይሰጣል፣ እንዲሁም በሌሎች አካላት የሚሰጡበትን አግባብ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፤
- ❖ ከኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ ከተለያዩ የስራ ክፍሎችና ከታችኛው አደረጃጀቶች ለሚቀርቡ የእገዛ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣል፤
- ❖ የመስሪያ ቤቱ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ሥራ ላይ መዋሉን፣ የፖሊሲ ዶክሜንቶች በአግባቡ መስራታቸውንና መያዛቸውን ይከታተላል፣
- ❖ የመስሪያ ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት አሰጣጥ በተጠቃሚዎች እንዲገመገም ያደርጋል ፤ ከተጠቃሚዎች ለሚነሱ የአሰራር ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል ፤
- ❖ ከኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ በመመሪያዎችና በአሰራር ማንዋሎች የተመላከቱ ስራዎችንና ከአስተዳደር ዘርፍ ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡